

# ከሄኖክ አየለ(የፊልም አዘጋጅ) ጋር እንጨዋወት

‹የአማርኛ ፊልም በጥሞና የሚያይ ሁሉ የሚያውቀው መራሒ፣ ሄኖክ አየለ ከቤታችን ጋር ማለፊያ ቆይታ ነበረው።›

በታደለ አያሌው | | 2015-09-28

## ፩) ትውልድ(ቀንና ቦታ)፣ ቤተሠብ፣ ትምህርት

የሐ፡- መግቢያችን የቤተሰብ ነገር ነው። አግብተሃል እንዴ ሄኖክ?

ሄኖክ፡- አዎ። አንድ ሦስት ዐመት ሆነን። አሁን እንዲያውም ልጅ እየጠበቅን ነው እልሃለሁ።

የሐ፡- ማን አልካት ስሟን?

ሄኖክ፡- ኧረ ታውቃታለህ። ትነበብ ተረፈ ትባላለች። ተዋናይት ነች። ‹‹ስስት››፣ ‹‹ይሉኝታ››፣ ‹‹ወርቅ በወርቅ›› እና ሌሎች ፊልሞች ላይ ተውናለች። ከእኔ ጋር ደግሞ፤ ‹‹ገመና ፩›› የቴሌቪዥን ድራማ ላይ እና ‹‹ፔንዱለም›› ፊልም ላይ እኔ አዘጋጅ እሷ ተዋናይት ሆነን አብረን ሰርተናል። ሌሎች የተወሰኑ ስራዎቼ ላይም በኤዲተርነት ሰርታለች።

## ፪) ሙያ፣ አስተዋጽዖ፣ ተሰጥዖ

የሐ፡- ያዘጋጀሃቸው ፊልሞችን እኔ ስቆጥር ፲፩ ደረሱ። እስኪ ፊልሞችህን አስቆጥረኝ።

ሄኖክ፡- ቁጠር። የመጀመሪያው ‹መስዋዕት›፣ ኹለተኛው ‹የወንዶች ጉዳይ፩›፣ ከዚያ ‹አልቦ›፣ ከዚያ ‹ፔንዱለም›፣ ከዚያ ‹ስብራት›፣ ከዚያ ‹ልክ ነኝ!›፣ ከዚያ ‹ይግባኝ›፣ ከዚያ በኋላ ‹ቀሚስ የለበስኩ 'ለት›፣ ቀጥሎ ደግሞ ‹አዲናስ› እና አሁንም ሌሎች ስራዎች ላይ ነኝ። ገመና፩ የቴሌቪዥን ድራማ ላይም በዝግጅት ነበርኩበት።

የሐ፡- እውነትም ልጆችህ ናቸው። አልፎ አልፎ ከፊልም ሰሪዎች የምታዘበው ‹‹ፊልሞቼ ልጆቼ ናቸው›› ካሉ በኋላ ዝርዝራቸውን እረሳሁ ሲሉ ነበር። እንዲህ በስስት ከነ ልደት ተራቸው መንገርህን አድንቂያለሁ። ያውም በድንገት፣ ባንድ ትንፋሽ!

ሄኖክ፡- በል እርምህን አውጣ፣ ፊልሞቼን መቼም አልረሳልህ። እንኳን ርዕሳቸው ይቅርና የቀረጻ ዉጣ ውረዳቸው፣ የተዋንያኑን ነገር፣ የቦታ ቦታው ነገር፣ የአጋሮች እገዛ፣ የእንቅፋቶች ከፍታ ሁሉ አልረሳቸውም እኔ። ጊዜ ኖሮህ ባጫወትኩህ።

የሓ፡- ለምን ዳይሬክተር ብቻ ሆንክ ግን፤ ያውም የፊልም ብቻ?

ሄኖክ፡- ሁሉንም ስለሚያካትት ነዋ። ዳይሬክተር ስለሆንኩ እኮ ተዋንያንንም፣ ደራስያንንም፣ ‹ፕሮዲዩሰሮችንም›፣ ሌሎችንም ቀድሞ የመምራት እድል አለህ። ስሜቴን፣ ሃሳቤን፣ ህልሜን አጋራበታለሁ። እና፤ ዳይሬክተር የሆንኩት አንድም ስለምወደው አንድም ስለምችለው ነው። ‹ለምን የፊልም ብቻ› ላልከው ግን እኔም እያሰብኩበት ነው። የተማርኩት እንዲያውም ቴአትር ስለሆነ፣ ወደ ፊት ቴአትርም አንድ መተንፈሻዬ እንደሚሆን እርግጠኛ ነኝ።

የሓ፡- ደግም እኮ የፊልም ዳይሬክተር በኛ አገር አይደግምም ይባል ነበር። አንተ ከመድገምም እስከ አስራ አንድ ፊልሞች ደጋገምክሳ። ምኑ ቢረዳህ ነው ያን ያህል?

ሄኖክ፡- ሌላም ስራ የለኝ እኔ። ሲደመር የምወደው ስራ ነው ፊልም። እና የመጀመሪያው ስራዬ ቀጣዩን እየጠራልኝ የመጣ ይመስለኛል። አንዳንዴ በምፈልገው ልክ ባልሰራም ለማቃናት እየሞከርኩ ቀጠልኩ። በተለይ ከ‹‹የወንዶች ጉዳይ›› ዝግጅት በኋላ እውቅናውና ግብዣዎች በዙ። እኔም ደጋገምኩ እንዲያ።

የሓ፡- ኹለት አባባሎች እሰማለሁ። ‹‹በኛ አገር፣ የፊልም እና የፊልም ሰሪ ባላገር የለውም›› አሉ?

ሄኖክ፡- ሃሳብህ ፊልም ሰሪዎች ሁሉ የአዲስ አበባ ኗሪዎች ብቻ ናቸው፤ ታሪክም ከዚያም ከዚህም እየተነሳ አይደለም ከሆነ በከፊል እስማማልሃለሁ። ምክንያቱም ከክፍለ ሃገር እንኳን የሚመጡ ባለሙያዎች ከመጡበት ይልቅ ይህን መሀሉን ነው የሙጥኝ የሚሉት። ያ የሆነው መሳሳታቸው እስኪታወቃቸው ድረስ ይሆናል። ነገር ግን አልፎ አልፎ አሉ። ለምሳሌ ‹እቴጌን› ያየህ እንደሆነ ጥርረቶች መኖራቸውን ታምናለህ። ያም ሆኖ ግን የኢትዮጵያ ፊልም እስከተባለ ድረስ ታሪኮች ከዚያም ከዚህም በሚዛናዊነት፣ ባለሙያዎችም ከዚያም ከዚህም በእኩልነት መነሳት እንዳለባቸው ይሰማኛል።

የሓ፡- ብዙዎች የፊልም ተዋንያን ሲሉ እንደሰማኋቸው፣ ወደ ፊልሙ የገቡት ባጋጣሚ ነው። ድንገት እንደዋዛ። አንዱ ‹‹ስታዲየም አካባቢ ሻይ ስጠጣ ዳይሬክተሩ አየኝና ወዶ አስጀመረኝ››፣ ሌላው ‹‹ቦሌ አካባቢ ታክሲ ስጠብቅ ለዚህ ፊልም ትመጥናለህ ተብዬ ጀመርኩ››፣ ሌላውም እንዲህ እንዲህ ይላል። አንተስ ሚና ለመስጠት ተዋንያንን ከየት ነው የምትፈልግ? በየ ከበባት ሙያውን ሲያዳብሩት ያደጉት ያሉበት ቦታ ነው? ይሁነኝ ብለው ከገቡበት ማሰልጠኛ ተቋማት አካባቢ ነው? ወይስ እንዲህ በየስርቻው?

ሄኖክ፡- ሁሉንም አማራጭ ነው እኔ የምጠቀመው። በጣም ኃላፊነት የሚሰማህ ከሆንክ ሰልጥነው ተሠብስበውበታል በሚባለው አካባቢ ትሄድና የፈተና ጥሪ ታደርጋለህ። ካልሆነ ግን በመንገድም ላገኝ እችላለሁ። ምክንያቱም ‹‹ዳይሬክተር ገጸ ባህሪ ነው የሚፈልገው›› ይባላል። ለምሳሌ የአበበ ባልቻን አመጣጥ ያየህ እንደሆነ ድንገት ነው። እና አጋጣሚውን መጠቀምም ክፋት የለውም ልልህ ነው። እኔም የማደርገው እንዲሁ ነው። ፊልም ልሰራ ስል ማስታወቂያ እሰራለሁ። በዚህ በዚህ መስፈርት ብዬ እጠራና እፈትናለሁ። እሰራለሁ።

የሓ፡- ለሙያው ግን የትኛው ክብርና ቁጭት ይኖረዋል? ለምኖ የመጣው ወይስ ተለምኖ የመጣው?

ሄኖክ፡- አይ ማንም አይለመንም። መለመንም የለበትም። አጋጣሚው እንዳለ አሳውቃለሁ እንጂ እባክህ አልልም። ያን ባላደርግ ጫናው ለራሴው ነው። እያንዳንዱን የቀረጻ ቋንቋ ሁሉ ማላመድ ይጠበቅብኛል እኮ። ስለ ሙያ ክብር ካነሳህ አይቀር እንዲያው ከዚህ ጋር አያይዘን ማውራት ካለብን ልንገርህ። አንዳንዴ የተማሩት ሰዎች የሚብሱበት ጊዜም አለ። ስለ ተማሩ ብቻ አልታዘዝም ይላሉ። ያኔ ትደነግጣለህ። እንዲሁ ከመንገድ የመጣው ደግሞ ያስደምምሃል። እና ዋናው ነገር ማስተዋል ነው።

የሓ፡- ደራሲዎችና ተዋንያን በፊልሞች ቁጥር ልክ የተለያዩ ናቸው። አንደኛው ላይ የነበረው ደራሲ እና ተዋንያን አብረውህ

ሌሎች ፊልሞች አይሰሩም። ይሁነኝ ብለህ ነው ወይስ አንዱ ፊልም ሲያልቅ ተጣልታችሁ ነው የምትለያዩ?

ሄኖክ፡- አይገርምህም አስቤው አላውቅም። ግን እየተጣላን አይደለም።

## ፫) መሰናከሎች፣ ማለፊያ ጥንካሬዎች

የሐ፡- -

ሄኖክ፡- -

## ፬) እሱን አጥተን እንዳናጣው ነገር

የሐ፡- ችሎታህን ፊልሞችህን ያዩልህ ይመሰክሩልሃል። ከዚያ በተረፈ ግን ‹‹ሄኖክ ወጣቶችን አግኝቶ የሚያውቀውን ለማካፈል አይሰለችም›› ይላሉ። እውን ከጀማሪዎች ጋር ጊዜ አለህ?

ሄኖክ፡- በጣም። የማስተማር ፍላጎትም በውስጤ ይሰማኛል። ይህን ሳደርግ እኔ እጠቀማለሁ። ከጀማሪዎች ጋር ስትወያይ ወደ ሙያው ለመግባት ያላቸውን ጉጉትና ፍቅር ሳይ እኔ ራሴ የማገኘው ወኔ አለ። ዞሮ ዞሮ እርካታው ለኔ ነው።

የሐ፡- አሁንስ ምን እየሰራህ ነው?

ሄኖክ፡- አንድ በቅርቡ የሚወጣ ፊልም አለ። ትንሽ Experimental ለማድረግ ለፍተንበታል። ከከተማው ግርግር ወጣ ብሎ ባዲስ መልክ ሊታይ የሚችል ስራ ነው። ጊዚያዊ ርዕሱ ‹ኦቺንታ› ይባላል። ኹለተኛው ደግሞ አሁን ወደ ቀረጻ እየገባንበት ያለ ፊልም አለ። በዚሁ ፳፻፫ዓ.ም. ራሴ ፕሮዲዩስ የማደርገው ፊልምም ይኖራል።

## ፭) መርሆች፣ የህይወት ፍልስፍናው

የሐ፡- ምርጫ ነው ቀጣዩ ጥያቄዬ። ባንተ እምነት ‹‹ፊልም ለስሜት በስሜት›› ወይስ ‹‹ፊልም ለልዕልና በእውቀት››?

ሄኖክ፡- በኹለቱ መሃል ነው መልሴ። ምክንያቱም ወይ ያልተገለጠልኝ ነገር ከሌለ በቀር ጥበብን በጥበብነቱ ብቻ ስትሰራው ሁሉንም ይይዝልሃል ባይ ነኝ። ደረቅ እንዲሆን አልፈልግም። ጥበብ የሚል ማዕረግ እስካለው ድረስ ለዛ ይፈልጋል። ‹‹እንዲህ እንውጣ!›› ‹‹እንዲህ እንግባ!›› የሚል ትዕዛት ከሆነ ምኑን ጥበብ ሆነው? አዕምሮ ውስጥ እንዲገባ፣ ገብቶ እንዲቆይ ካስፈለገ ቅመም ያስፈልጋል። ስሜት-ጥበብ። ከዚያ በተረፈ ግን የእውነት የጥበብ ሰው ከሆንክ መምረጥ አይጠበቅብህም። ለስሜቴ ብቻ ለልማቱ ብቻ አትልም። አጋጣሚዎችን ሰው እንዲያይልህ ትጠበባለህ እንጂ።

የሐ፡- እድሜህን ስታስብ፤ እያለቀብህ ይመስልሃል ወይስ በሚገባ እየተጠቀምከው እንደሆነ ይሰማሃል?

ሄኖክ፡- ይደበላለቃል። አንዳንዴ አንድ ትንሽ ልጅ ተአምር ሲሰራ ሳይ እድሜዬ ላይ እንደተጫወትኩ ይሠማኛል። በአዘቦት ግን የሠራኋቸውን ነገሮች ዞር ብዬ ሳይ ደግሞ ተመስገን እላለሁ። እና፤ ለመጽናናትም ለመጸጸትም ማስተያየት ያስፈልጋል።

የሐ፡- ከማን ጋር ነው የምታስተያይ? ማን ነው በትልቅነቱ የሚገርምህ ሰው?

ሄኖክ፡- ብዙ ናቸው። ቀድሞ የሚመጣልኝ ግን ሱራፌል ወንድሙ ነው። አንድ ወቅት ‹ሆሊ ላንድ› አስተምሮኛል። እና ያለው

ተሰጥኦና ችሎታውን ደግሞ የሚገልጥበት መንገድ ግሩም ነው። ሌሎችም አሉ። በተለይ በሸገር ሬዲዮ፣ ‹‹የጨዋታ እንግዳ›› ላይ የሚቀርቡ ሰዎች ሁሉ ይገርሙኛል። እነሱን ሳውቅ ነው የቤት ስራዬን የማከብደው እንዲያውም።

የሓ፡- አንዳንድ የሬዲዮ ዉይይቶች ላይም እኔና አንተ ተገናኝተን ስናወራም የታዘብኩህ፣ መሃል ቤት ነህ። ‹‹ልክ ነው›› ወይ ‹‹ልክ አይደለም›› ሳይሆን በመሃሉ ነው የምትገኝ። አስተያየት ላይ ወዴት ነህ?

ሄኖክ፡- እንዳልከው ነው። አሁን ለምሳሌ አንድ ሰው መጥቶ ‹‹የኢትዮጵያ ፊልም የሞተ ነው›› ቢለኝ ላለመሞቱ ማስረጃ አመጣለሁ። በተቃራኒው ደግሞ ‹‹የኢትዮጵያ ፊልም አድጎ ጨርሷል›› የሚል ሰው ቢመጣ ደግሞ ምን ምን እንደሚቀረው እዘረዝርለታለሁ። እና በኔ እምነት ጨለማ ብቻ አይታየኝም፣ ብርሃን ብቻም ያለ አይመስለኝም። ኹለቱም አሉ። እኔም አስተያየት ላይ የትኛውም ጽንፍ ብቻውን የለም ባይ ነኝ። ወደ መሃል መምጣት ያስፈልጋል።

የሓ፡- ሌላ ጊዜ ጥያቄዎች ሲኖሩን እፈላልግሃለሁ። በየሓ ቤተ ጥበብ ሃሳብ ደስተኛ ነህ እንደውል?

ሄኖክ፡- ሲጀመር ሃሳቡ የተስማማኝ ቤት ነው። ሰው አተኩሮ ቢያስብ ለካ እንዲህም አለ። እና እንዳወራንበት ከገፋችሁበት ብዙ ያስኬዳል። እኔም ስተደውሉልኝ ብቻ ሳይሆን እኔው ራሴ ፈልጌ የምሳተፍበት ቤት ነው። ብቻ ወደ ፊት!

የሓ፡- እናመሰግናለን፣ ሄኒ።

ሄኖክ፡- እኔም።

## ፮) ምንጮቻችን

ቀጥተኛ ቃለ ምልልስ፣ የሓ ቤተ - ጥበብ